# የበዓሉ ትዝታ

እ| ነይ በመስከረም
እንደ በዓሉ
አወጋሻለሁና የገባን
ጋራ ሸንተረሩን
አወስድሽና ሱጴ
የበዓሉን ሀገር
የሱጴቦሩን ሚስጥር
ዓይነግቡ የሆኑ
የዋርካዎቹን ነገር
የጉጉ መለኮ| ን
የእርግቦቹን ሠፈር
በል ልቤ ተናገር
የገዘፈ እንደዋርካ
መቼ ገና ተነካ
የልቤ ምቱ ጨመረ
በዓሉ ተናገረ
እውነትን መሰከረ
በሕሊና ደወል
በአድማስ ባሻገር
ድንግል መሬት
ውብ ሀገር ሃዲስ ምድር
የበዓሉ ትዝታ የበዐሉ ሠፈር
አንት የሱጴ ተክል
አንት የዘንባባ ፍሬ
የኢሉ ፍራፍሬ
ዶቅማ ትርንጐ ሮማን
አንቺ ብሩክ ማሕፀን
ወልዶሻል ብዕረፈጣን
ያ በዓሉ ልጅሽ ተዋግቷል በብዕሩ
ያገር ፍቅር ነው ድንበሩ

እውነት ነው ምስክሩ
ለኔ ሳይል ለወገኑ
እርሱ ብርሃን መሆኑ
አንፀባራቂው እንቁ

በ
በ ዓ ሉ
ሉ

በብዕር ተወራረደ
እርሱ እንደጧፍ ነደደ
በቀይ ኮከብ ጥሪ
በቀይ ኮከብ ዘመቻ
በጦሩ ሜዳ ዛሬም የለውም አቻ
እንደነሀስ አገደ
ብዕሩ የሳት ላንቃ
ጠላቱን የሚወቃ
በነሀስ ፍላፃ ፀሐፊ
ብዕሩ ተናደፊ
እንደጅራፍ ገራፊ
የደራሲያን ፋና ወጊ
እንደወታደር ተዋጊ
በዓሉ ሩቅ አላሚ
ቅርብ አዳሪ
የተሳለ ፍላፃ ወርዋሪ
በብዕሩ ከዘመን ዘመን ተሻጋጋሪ

ከአፀደ ለንጮሳ
ጅማ - ኢትዮጵያ